ሁኔታዎች ተገደና ከሁሉም በላይ ደግሞ የተቃዋሚያችን ሰፈር ብትንትኑን አውጥተውለት ከሱ ሊደባለቁ የሚፈልጉ ሃይሎች 'ተደራድረንና ታግለን አንዳንድ ኩንሴሺኖች አስገኘን' ለማለት እንዲመቻቸውና የማደናገር ተልእኳቸው ይበልጥ እንዲሳካ አንዳንድ ኩንሴሽኖች ያደርግም ይሆናል:: ግን ይኸ ምንም የሚቀይረው ነገር አይኖርም:: ሰሞኑን እነበየነ 'ድምጻቸውን ከፍ አርገው' አንዳንድ ጥያቄዎች ማቀረብ መጀመራቸው፣ ካምፔኑን 'ለማማሟቅ' ሆን ብለው የሚሰነዝሩት ማደናገሪያ ከመሆን አልፎ የሚሄድ ነገር አይደለም:: የሃቀኛ ተቃዋሚዎች መመዘኛ አሁን ሁኔታው ካልተሟላ ምርጫ ውስጥ አንገባም፣ መቶ በመቶም ባይሆን ወያኔ እነዚህን እነዚህን የህዝብ ጥያቄዎች መመለስ አለበት ይህ ካልሆነ በመጨረሻው ሰዓት ብቻ ነው ሁኔታውን ከሌሎች ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ጋር ገምግመን መሳተፍ አለመሳተፋችንን የምንወስነው የሚል መሆን አለበት:: የመጣ በመጣ አንዷት ወንበርም ብትሆን ብናገኝ እንሳተፋለን እያሉ በይፋ እየተናገሩ፣ ከሌሎች ተቃዋሚዎች ጋር ሳይሆን ብቻችንን የምንወስነው ነገር ነው እያሉ 'ቅድሚያ ሁኔታዎች' እያሉ ቢደረድሩ እንኳን ሂደታቸው ምንም ተዓማኒነት አይኖረውም::

ይህንን የግንቦት ግርግር ከረዥም ጊዜ የዲሞክራሲ ትግላችን አኳያ እንመርምረው ካልን ለአንዲት ሰኩንድ እንኳን የህድረ ግንቦትን ሁኔታ በአእምሯችን መቃኘት አለብን:: ይህ ምርጫ የተመድ ኤክስፐርቶች ለተጭበረበሩ የምርጫ ሂደቶች አለሳለሰው በሰጡት መጠሪያ መሠረት 'ፊዘለት አር የንትድ' ነው:: ማለትም የሚሰጠው ውጤት ከወዲሁ ምርጫውን ይጠቀመናል ብሎ፣ ለሱ እንደሚጠቅም አርጎ በሚያዘጋጀው ኃይል በቅድሚያ የተወሰነ ውጤት ነው:: በነገው የወያኔ ፓርላማንት ውስጥ የሚሰየሙት ተቃዋሚዎች ቁጥር ከወዲሁ በወያኔ የተወሰነ ነው:: ይህ ቁጥር አስርም፣ ሃያም አምሳም ከዚያም በላይ ሊሆን ይችላል:: ህዝብ ለማደናገር፣ ተቃዋሚዎችን ለመከፋፈል፣ ነጻ ምርጫ ተካሂዷል ለማስኘት የሚያስፈልገውን ያህል ለወያኔ ተቃዋሚዎች ወያኔ የሚያስፈልገውን ወንበር ይለቃል:: ይህንን ለማድረግ የሚያደፋፍረው ደግሞ የፊዘለት አር የንትድ ምርጫዎች ሌላ ገጽታ ነው:: አዘጋጁ ኃይል በፓርላማንት ውስጥ የሚቃወሙትን ኃይሎች ከወዲሁ በመወሰን አይመለስም:: የተቃዋሚነት ሚናቸውንና ልካቸውንም የሚወስነው ራሱ ገዥው ኃይል ነው:: ከዚህ ሃቅ ተነስተን የህድረ ግንቦትን ሁኔታ ብንቃኝ ገልጽ ስእል ይኖራል::

በወያኔ መልካም ፈቃድ ቁጥራቸውና ሚናቸው ተወስኖላቸው በተቃዋሚነት ስም እነዚህ ሰዎች ፓርላማንት ውስጥ ስለተሰየሙ ብቻ በቅድመ ግንቦት ወቅት ከነበራቸው ሌላ ራእይ አይኖራቸውም:: እስካሁን ካሳዩት የተለየ የትግል ወኔ አይላበሱም:: እርግጥ በስነሥርዓት አድማቂነት ተሰልፈዋልና አሁን የምርጫ ካምፔይኑን ለማማሟቅ የሚያሰሙት ተቃውሞ ዓይነት "የመድበለ ፓርቲውን" ፓርላማንት ህይወት ለማማሟቅ የወያኔ የራሱ ጋዜጠኞችና ማስ ሚድያ እያደመቀ እያገነነ የሚናገርለት 'የተቃዋሚ' ግርግር ትርኢት ሊኖር ይችላል:: ነገር ግን የሃገራችን ችግሮች ከናው ጋር እንዳሉ ይቀያሉ:: ሻማ ያዥዎችና ሥነስርዓት አድማቂዎች ደሞ እንደተለመደው ለሌላ የምርጫ ሰሞን ግርግር ዙር አምስት ዓመት ጠብቀው እስኪባንኑ ድረስ ትግሉ መቀጠል ይኖርበታል:: ይህንን ለመቀጠል የሚችሉት ደግሞ ከዛሬው 'ከግንቦትም በኋላ ህይወት አለ' ብለው ለመጭው ትግል በወጉ የሚዘጋጁ ዲሞክራቶች ናቸው::

ከግንቦት በኋላም ሃገራችን ከነአስር ሺ የፖለቲካ እስረኞቿ፣ ከነተጫነባት የዘፈቀደ አገዛዝ፣ ከነሚሊዮን ርሃብተኞቿ፣ ህዝቦችን ከህዝቦች ለማናከስ ሆን ተብለው ከተቀበሩት ጊዜ ጠብቀው የሚፈነዱ ቦንቦች ...ወዘተ ትኖራለች:: እነዚህም የሚወልዷቸው ትግሎች ይኖራሉ:: ዋናው ጥያቄ የሃገራችን ዲሞክራቶች ከዚህ ሁኔታ አንጻር ምን ያደርጋሉ የሚለው ነው::

ሳው ደግሞ ' መኢሶን ሊቆጣጠረው የሚችል ኃይል አገር ውስጥ ከአብኮ ጋር ተባብሮ ሊፈጥር ላይ ታች እያለ ነው' የሚል እርግጠኛ ድምዳሜ ላይ ደርሷል:: ኢህአፖም ኢህአፖ ነው:: ባጭሩ ቢከፋም ቢለማም በሃሳቡም፣ በገንዘቡም በመድከሙም ደረጃ ከና ውጭ በማንም ላይ የምንተማመንበት ሁኔታ የለም::

ትልቁ ችግር ለጉባኤው ይገኛል ብለን ያሰብነው ገንዘብ አለመገኘቱ ነው:: በተለያዩ ምክንያቶች:: ነገር ግን በምንም ዓይነትና ከግንቦት በፊት መደረግ አለበት ብለን ከድህነትና ከጊዜ ጋር አሽቀድድም ላይ ስለሆንን ይህንን ጉባኤ በብድር ከማካሄድ ሌላ ምንም መፍትሄ አላገኘንም:: እንደታሰበው 600 ሰው ያህል ለሰስት ቀን ለማድረግ ባይቻል የክልልና የብሄረሰብ ስብጥሩ እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ሰስት መቶ ሰው ለሁለት ቀናት ብቻ ለመሰብሰብ አቅደናል:: ብድር የተባለው አዛው እናው በናው ሲሆን ለቀስተ ደመና ሬድዮ አስከችላይ/አገሰት ካለን በጀትና ከአንድ ጓድ ብድር አንድ አስር ሺ ደላር ያህል ለማውጣት መድበናል:: ይህንን ለማካካስ በቅርቡ በምናውቃቸውና ትግላችንን ይደግፋሉ ብለን በምንተማመንባቸው ኢትዮጵያውያን ዙሪያ በመ አባላትና ደጋፊያች ትብብር የፈንድሬዚንግ ካምፔይን ለመጀመር አስፈላጊውን ዝግጅት አርገናል:: የተዘጋጁት የርዳታ መሰብሰቢያ ቅጾች በአስር ቀን ውስጥ ይደርሷችኋል::

አሁን ያለንበት ሁኔታ ይኸንን ይመስላል:: ተወያዩና በሃሳብም በአቅምም ልትተባበሩ የምትችሉበትን ሁኔታ አስታውቁን::

01/04/00